የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፳፻፬ ዓ. ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Fourth Year No. 30
ADDIS ABABA 18 February 2012

ማውጫ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ
--------------------ገጽ

CONTENTS

**Addis Ababa City Government Food, Medicine and Health Care Administration and Control Authority Establishment Proclamation**
-------- pages

### አዋጅ ቁጥር ፴/፳፻፬

### የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና፣ የጤና ክብክቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ

የአዲስ አበባን ነዋሪ ደህንነቱ ፈዋሽነቱ እና ጥራቱ ካልተረጋገጠ ዘመናዊም ሆነ ባህላዊ መድኃኒት መጠበቅ ያለበት በመሆኑ፤

በከተማዋ በተለያዩ መንገዶች ለህብረተሰቡ ከሚቀርብ ምግብ የሚመጣ ለጤና አደገኛ ከሆነ የምግብ መመረዝና ብክለት መከላከል በማስፈለጉ፣

ደረጃውን ባልጠበቀ የጤና አገልግሎት እንዲሁም ብቃትና ሙያዊ ሥነ-ምግባር በጎደለው የጤና ባለሙያ፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅና በተላለፊ በሽታዎች ቁጥጥር ጉድለት ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን የጤና ችግር መግታት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬/፩/ሀ/ እና የፌደራል መንግስት የምግብ መድኃኒትና ጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፩/፳፻፩ ዓ.ም አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

### Proclamation No. 30/2012

### A Proclamation to Establish the Addis Ababa City Government Food, Medicine and Health Care Administration and Control Authority

WHEREAS, it is necessary to protect the Addis Ababa City residents from unsafe, inefficacious and poor quality modern and traditional medicines;

WHEREAS, it is found necessary to prevent from food poisoning and contamination which is hazardous to health and caused by food supplied to the public in the City in different ways;

WHEREAS, it is necessary to avert health problems due to substandard health institutions, incompetent and unethical health professionals, poor environmental health and communicable disease;

NOW, THEREFORE in accordance with Article14(1) (a) of the Revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No.361/2003,and Article 55(1) of the Federal Government Food, Medicine and Health Care Administration and Control Proclamation No.661/2009 the City Council proclaimed as follows:-

ያንዱ ዋጋ 10.10
Unit Price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ‹‹ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴/፪ሺ፬›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. ‹‹አዋጅ›› ማለት የፌደራል መንግስቱ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፩/፪ሺ፪ ነው፤

፪. ‹‹ምግብ›› ማለት ማንኛውም በጥሬነቱ፣በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀ ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለህብረተሰቡ አገልግሎት ቀርቦ ለሰው ምግብነት የሚውል ነገር ሲሆን ውኃ ወይም ሌላ መጠጥ፣ የሚታኘክ ማስቲካ፣ ተጨማሪ ምግብ እንዲሁም ምግብ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማከምና ማንኛውም ንጥረ ነገር የሚያካትት ሆኖ ትንባሆና ለመድኃኒትነት ብቻ የሚያገለግሉ ንጥረ ነገሮችን አይጨምርም፤

፫. ‹‹መድኃኒት›› ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለማስታገስ ወይም ለመከላከል የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን፣ ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን፣ የባህል መድኃኒቶች፣ ተደጋጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒቶች፣ መርዞች፣ ደምና የደም ተዋጽኦዎች፣ ቫክሲኖች፣ ጨረር አፍላቂ መድኃኒቶች፣ ኮስሞቲኮች፣ ሳኒተሪ ዝግጅቶች እና የሕክምና መሣሪያዎችን ይጨምራል፤

፬.‹‹የጤና ባለሙያ›› ማለት የሰውን ጤና ለመጠበቅ ወይም አገልግሎት ለመስጠት አግባብ ባለው አካል እንደ ጤና ባለሙያ የተመዘገበ ሰው ነው፤

## Part One
## General

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Addis Ababa City Government Food, Medicine and Health Care Administration and Control Authority Establishment Proclamation No. 30/2012."

### 2. Definition

In this proclamation unless the context otherwise requires:-

1. "Proclamation" means the Federal Government Food, medicine and health care Administration and control Authority Establishment Proclamation No 661/2011."
2. "Food" means any raw, semi-processed or processed substance for commercial purpose or to be served for the public in any way intended for human consumption that includes water and other drinks, chewing gum, supplementary food and any substance which has been used in the manufacture, preparation or treatment of food, but does not include tobacco and substances used only as medicines;
3. "Medicine" means any substance or mixture of substances used in the diagnosis, treatment, mitigation or prevention of a disease in human and includes narcotic drugs, psychotropic substances and precursor chemicals, traditional medicines. Complementary or alternative medicine, poisons, blood and blood products, vaccine radio active pharmaceuticals, cosmetics and sanitary items and medical instruments;
4. "Health professional" means a physician who is licensed by the executive organ to examine and diagnose human disease and treat them by drug or surgical operations or any other health professional who is authorized to perform such activities;

፭.‹‹የህክምና ባለሙያ›› ማለት ሕመምተኛውን በመመርመር የበሽታውን ዓይነት ወይም አካልን በመቅደድ የሚያክም የሰው ሐኪም ወይም እነዚህኑ ተግባራት እንዲያከናውን በሚመለከተዉ አካል የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ ነው፤

፮.‹‹የጤና ተቋም›› ማለት የጤና ማበልጸግ፣ የበሽታ መከላከል፣ ማከምና መልሶ ማቋቋም ሥራዎችን ወይም የመድኃኒት ንግድ ሥራን ወይም አገልግሎት የሚያከናውን ማንኛውም የመንግስት፣መንግሥታዊ ያልሆነ ወይም የግል ተቋም ነው፤

፯. ‹‹ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም›› ማለት ማንኛውም የኅብረተሰብ መገልገያ ተቋም ሲሆን፣ ትምህርት ቤት፣ ማረሚያ ቤት፣ የአረጋዊያን መንከባከቢያ ማዕከላት፣ መዋዕለ ህፃናት፣ የገበያ ቦታዎች፣ የስፖርት ቦታዎች፣ የመታሻ ማዕከላት፣ የመዝናኛ ማዕከላት፣ የምግብ ማምረቻና ማዘጋጃ ቦታዎች፣ የፀጉር ቤቶችና የውበት ሳሎኖችን ይጨምራል፤

፰. ‹‹የመድኃኒት ባለሙያ›› ማለት አግባብ ባለው አካል የሙያ ስራ ፍቃድ የተሰጠው ፋርማሲስት፣ ድራጊስት ወይም ፋርማሲ ቴክኒሻን ነው፣

፱. ‹‹የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት›› ማለት በወጣው የጤና ቁጥጥር ደረጃ መስፈርት መሠረት በምግብ፣ በመድኃኒት ወይም በጤና ወይም በጤና ነክ አገልግሎት ወይም የንግድ ሥራ ለሚሰማራ ሰው የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነው፣

፲. ‹‹የሙያ ሥራ ፈቃድ›› ማለት የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ወይም ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማመርከት እንዲችል ለጤና ባለሙያ የሚሰጥ የምክር ወረቀት ነወ፣

፲፩.‹‹ከተማ›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፣

፲፪.‹‹ባለስልጣን›› ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቋቋም የአዲስ አበባ ከተማ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብክቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፣

፲፫. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ለሴትም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፣ዓላማ፣ አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር

### ፬. መቋቋም

፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ከዚህ በኋላ «ባለስልጣን» ተብሎ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለው መንግስታዊ መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁማል፡፡

5. “Medical practitioner” means a physician who is licensed by the concerned organ to examine and diagnose human diseases and treat them by drug or surgical operations or any other health professional who is authorized to perform such activities;

6. “Health institution” means any governmental, non-governmental or private institution that carry out promotive, preventive, curative and rehabilitative or medicine trade or services;

7. “Health related controllable institution” means any public place including schools, prisons, day care centers, geriatric centers, or pnanage centers, nurseries, market place, gyms, massage centers, recreation centers, food producing and processing areas, barber and beauty salons;

8. “Pharmacy professional “means a pharmacist druggist or pharmacy technician licensed by an appropriate organ;

9. “Certificate of competency” means a work license issued for a person to carry out food, medicine, health or health related services or trade in accordance with standards set;

10. “License” means a Certificate issued for a health professional to provide medical or other health related services;

11. “City” means Addis Ababa City;

12. “Authority” means the Addis Ababa City Food, Medicine and Health Care Administration and Control Authority established in accordance with this proclamation;

13. “Person” means any physical or juridicial person.

3. In this Proclamation, unless the context require otherwise, any expression in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## Part two

## Establishment, Objectives, Organization, Powers and Functions

### 4. Establishment

1. The Addis Ababa City Government Food, Medicine and Health Care Administration and Control Authority (hereinafter referred to as the “Authority”) is hereby established as an autonomous government office having its own legal personality;

፪. የባለስልጣኑ ተጠሪነት ለከተማው ከንቲባ ይሆናል፡፡

**፭. *ዋና መስሪያ ቤት***

፩.የባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ በማዕከል ይሆናል፡፡

፪.በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ደረጃ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፣

**፮. *ዓላማ***

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

በአዲስ አበባ ከተማ የምግብ ደህንነትና ጥራትን፣ የመድኃኒት ደህንነት፣ ፈዋሽነት ፣ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀምን የጤና፣ የህክምናና የመድኃኒት ባለሙያዎችን ሙያዊና የስነ-ምግባር ብቃትን፤የጤና ተቋሞችን ድርጅታዊ ብቃት እና የሃይጅንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ለግልና ለህብረተሰብ ጤና ተስማሚ መሆኑን በማረጋገጥ የተጠቃሚውን ጤንነት መጠበቅ ይሆናል፡፡

**፯.*የባለስልጣኑ አቋም***

ባለስልጣኑ፡-

፩. በከተማ ደረጃ

ሀ. የጠቅላላ ጉባኤ

ለ. የስራ አመራር ቦርድ

ሐ. ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና

መ. አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፪. በክፍለ ከተማ ደረጃ

ሀ. ጽህፈት ቤት

ለ. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

ሐ. አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል

፫. በወረዳ ደረጃ

ሀ. ጽህፈት ቤት

ለ. አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል

**፰. *የባለስልጣኑ ሥልጣንና ተግባር***

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

፩. የምግቦችን ደህንነትና ጥራት፣ የመድኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነት፣ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀም የህክምና ባለሙያዎችን ብቃትና አሰራር፣ የኃይጅን፣ የአካባቢ ጤናን እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት የቁጥጥር ደረጃዎች ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤



2. The Authority shall be accountable to the Mayor of the City.

**5. *Head Office***

1. The Authority shall have its head office at the City level , and
2. It shall have offices at sub city and wereda level.

**6. *Objectives***

The objectives of the Authority shall be:-

To protect the health of consumers in Addis Ababa City by ensuring; food safety and quality, the safety, efficacy, quality and proper use of medicines, competence and ethics of health professionals, medical practitioners and pharmacy professionals, the standard of health institutions; and the hygiene and environmental health protection suitability for individual and community health.

**7. *Organization of the Authority***

The Authority shall have

1. At city level
   a. General Assembly
   b. Managing Board
   c. General director and deputy general directors and
   d. Necessary staff
2. At sub city level
   a. Office
   b. Executive committee and
   c. Necessary staff
3. At wereda level
   a. Office and
   b. Necessary staff

**8. *Powers and Functions of the Authority***

The Authority shall have the following powers and functions to:-

1. Ensure the safety and quality of food, safety of efficacy quality and proper use of medicines, competence and work procedure of health professionals, hygiene, environmental health and fulfillment of standards of control in health and health related institutions.

፲፩. የስነምግባር ግድፈት በሚያሳዩ የጤና ባለሙያዎች ላይ ተገቢውንእርምጃ ይወስዳል፤

፲፪. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ ያደራጃል፤

፲፫. በከተማው አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች ህግ መሠረት የባለስልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል ያስተዳድራል ያሰናብታል፤

፲፬. የጠቅላላ ጉባዔው ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፤

፲፭. ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፤

፲፮. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል ይከሰሳል፤

፲፯. በከተማ በክፍለ ከተማና ወረዳ ያለው የቁጥጥር ስራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን ለማድረግ ለክፍለ ከተማና ለወረዳ የምግብ፣ የመድኃኒት የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

**፱.የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩. ዋና ዳይሬክተሩ የባለስልጣኑ አስፈፃሚ በመሆን ባለስልጣኑን በበላይነት ይመራል፣ያስተዳድራል፤

፪. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፣

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፰ የተመለከተውን የባለስልጣኑን ስልጣንና ተግባሮች ስራ ላይ ያውላል፤

ለ. የባለስልጣኑን አመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለከንቲባ ያቀርባል፣ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

ሐ. ለባለስልጣኑ በተፈቀደለት በጀትና የስራ ዕቅድ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

መ. ባለስልጣኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ባለስልጣኑን ይወክላል፤

፫. ዋና ዳይሬክተሩ ለባለስልጣኑ የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

11. take necessary measure against health professionals who commit breach of ethics.
12. organized quality control laboratory necessary to carry out its duty;
13. employ administer and dismiss personnel of the Authority in accordance with the civil service law of the City Government;
14. serve as the secretariat of the general assembly;
15. collect appropriate payment for services it renders;
16. Own property, conclude contract sue and be sued in its name;
17. provide the necessary support to sub city and Wereda food medicine, health care administration and control office with a view to harmonizing the city, sub city and Wereda regulatory system.

**9. *Powers and Functions of the Director General***

1. The Director General being the chief executive officer of the Authority, shall direct and administer the activities of the Authority;
2. Without prejudice to the generality of the provision of sub article (1) of this Article, the Director General shall;
   a. implement power and function of the Authority specified under Article 8 of this proclamation;
   b. prepare and submit to the Mayor, annual and budget plan of the Authority and implement the same upon approval;
   c. effect payments in accordance with the approved budget and work plan of the Authority;
   d. represent the authority in its dealing with third parties;
3. The Director General may delegate part of his powers and functions to Deputy Director Generals and employees of the Authority to the extent necessary for efficient performance of the Authority.

***፲.የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባራት***

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፡-

፩.የባለስልጣኑን ተግባራት በማቀድ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛል፤

፪.በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል፤

***፲፩. የባለስልጣኑ ስራ አመራር ቦርድ ስልጣንና ተግባር***

የስራ አመራር ቦርድ፡-

፩. ባለስልጣኑ የሚቆጣጠራቸው ተቋማት ደረጃቸውን ጠብቀው በተቀናጀ መልክ መስራታቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል፤

፪. ከደንብና መመሪያዎች አፈፃፀም ጋር ተያይዘው በሚነሱና አመራር በሚሹ ጉዳዮች ላይ እንደ አግባቡ ውሳኔ ይሰጣል ወይም ከአስተያየቱ ጋር ለከንቲባው እንዲቀርብ ያደርጋል፤

፫. የባለስልጣኑን መዋቅርና የሰው ኃይል ኘላን መርምሮ ያፀድቃል፤

፬. ለከንቲባው የሚቀርበውን የባለስልጣኑን የስራ ኘሮግራም፣ በጀትና የአፈፃፀም ሪፖርት ያፀድቃል፤

፭. በዋና ዳይሬክተሩ በሚቀርቡለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል ይወስናል፡፡

***፲፪.ስለ ቦርድ አባላት***

፩. የሥራ አመራር ቦርዱ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራን በማስፈፀም ረገድ ጉልህ ሚና ካላቸው የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ፣ የጠቅላላ ጉባዔው አባላት ከሆኑ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጣ ሆኖ ሰብሳቢውን ጨምሮ በከንቲባው የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፤

፪. ቁጥራቸውም እንደ አስፈላጊነቱ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

***፲፫. ስለስራ አመራር ቦርድ ስብሰባ***

፩. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤

፪. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

***10. Powers and Functions of Deputy Director General***

The Deputy Director General shall;

1. assist the Director General in planning, organizing, directing and coordinating the activities of the Authority; and
2. perform other activities specifically assigned to him by the Director General.

***11. Power and Function of the Managing Board***

The board shall:-

1. supervise and control intuitions under supervision of the Authority;
2. decide on matters arising out of execution of regulation and directives that require direction or submit same to the Mayor with its opinion;
3. approve the structure and humane resource plan of the Authority upon investigation;
4. approve implementation plan budget and report submitted to the mayor;
5. deliberate on and decide issues that are submitted by the Director General.

***12 Members of the Board***

1. The board shall be composed of persons extracted from the executive and municipal service organs of the City Government, members of the the general assembly, non-government organs who are concerned with food, medicine, health care administration and control; the members, including the chair person shall be appointed by the Mayor;
2. Their number shall be determined, as may be necessary, determined by regulation to be issued to implement this proclamation.

***13. Meeting of the Board***

1. The shall meet one in month provided however that emergency so requires it may meet at any time at the call of chair person;
2. There shall be quorum if more than half of the members are present;

፫. ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፡ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፤

፬. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፣ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

***፲፬.የጠቅላላ ጉባዔ አባላት***

የምግብ ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ነክ በሆኑ አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የሚመክር በከተማው ከንቲባ ሰብሳቢነት የሚመራ የሚከተሉት አካላት የሚኖሩት ጠቅላላ ጉባዔ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣

፩.የከተማው ዋና ሥራ አስኪያጅ
፪.የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ
፫.የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከል ዳይሬክተር
፬. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ዳይሬክተር
፭.የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ዳይሬክተር
፮. የጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ
፯. የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ
፰. የፍትህ ቢሮ ኃላፊ
፱. የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዳይሬክተር
፲. የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር
፲፩. የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈሚዎች
፲፪. የግል ሆስፒታሎች ማህበር ሰብሳቢ
፲፫. የፋርማሲ ባለሙያዎች ማህበር ሰብሳቢ
፲፬. የላብራቶሪ ሙያ ማህበር ሰብሳቢ
፲፭. የሐኪሞች ማህበር ሰብሳቢ
፲፮. የነርሶች ማህበር ሰብሳቢ
፲፯. የህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ማህበር ሰብሳቢ
፲፰. የእንስሳት ህክምና ማህበር ሰብሳቢ
፲፱.የግል ክሊኒኮችና የምርመራ ማዕከላት ማህበር ሰብሳቢ
፳. የመድኃኒት ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች ማህበር ሰብሳቢ
፳፩. የባህል ህክምና አዋቂዎች ማህበር ሰብሳቢ
፳፪. የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ሰብሳቢ
፳፫. የአዲስ አበባ ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ
፳፬.የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ፎረም ሰብሳቢ
፳፭.የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ኘሬዝዳንት
፳፮.የሆቴሎችና ሬስቶራንቶች ማህበር ሰብሳቢ

3. The board shall pass its decision by majority vote in case of a tie, however, the chairperson shall have casting vote;
4. Notwithstanding the provisions of this Article the Board may issue its meeting procedure.

***14. Members of General Assembly***

The general assembly which deliberate on matters related to by the food medicine healthcare and control, which is chaired by the Mayor and composed of the following members, is hereby establishshed proc lamation;

1. Chief Manager of the City
2. Head of Bureau of Trade and Industry Development
3. Director of Occupational Competency Assessment and Certification Center
4. Director of Technical and Vocational Education and Training Agency.
5. Director of Higher Education Commission Relevance and Quality Agency
6. Head of Bureau of Health
7. Head of Bureau of Culture and Tourism
8. Head of Justice Bureau
9. Director of Environmental Protection Authority
10. Commissioner of Addis Ababa Police Commission,
11. Chief Executive of sub city
12. Chairperson of private Hospitals Association.
13. Chairperson of pharmacy professionals Association
14. Chairperson of Laboratory profession Association
15. Chairperson of physicians Association
16. Chairpersons of Nursing Profession Association
17. Chairperson of Public Health professionals Association
18. Chairperson of veternary Association
19. Chairperson of Private Clinics and Diagnostic Centers Association
20. Chairperson of Drug Retailers Association
21. Chairperson of Traditional Medicine Practitioners Association
22. Chairperson of Addis AbabaYouth Association
23. Chairperson of Addis Ababa Women Association
24. Chairperson of Addis Ababa Residents Forum
25. President of Addis Ababa Chamber of Commerce
26. Chairperson of Hotels and Restaurants Association

፳፬. የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተርና የሥራ አመራር ቦርድ አባላት

፳፭. የአዲስ አበባ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ዩኒየን ሰብሳቢ

፳፮.የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ

፳፯.ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ በከንቲባው የሚሰየሙ አባላት

## ፲፭.የጠቅላላ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

ጉባኤው፡-

፩. ባለሥልጣኑን በፖሊሲና ስትራቴጂክ ነክ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፤

፪. እንደ አስፈላኒነቱ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፤

፫. የባለስልጣኑን አመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርትና ሌሎች መረጃዎች ላይ በመመስረት አስተያየቶችን ያቀርባል፡፡

## ፲፮. የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች

፩. የጠቅላላ ጉባዔው መደበኛ ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ ይሆናል፣ ሆኖም በማንኛቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፤

፪. ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

፫. የጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ያልፋል፣ ሆኖም ድምፅ እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤

፬. የራሱን የስብሰባ ስነ- ሥርዓት ውስጠ ደንብ ያወጣል፡፡

## ፲፯. የክፍለ ከተማ ፅህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር፣

፩. የክፍለ ከተማውን የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የስራ ኘሮግራም በማዘጋጀት ለክፍለ ከተማው የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፪. በፌደራል መንግስት ደረጃ ተዘጋጅተው ከከተማው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው የቀረቡትን የቁጥጥር ደረጃዎች ያስፈፅማል፤



24. Director General and members of Managing Board of the Authority
25. Chairperson of union of Consumer Associations
26. Manager of Addis Ababa Water and Sewerage Authority
27. Other members to be appointed by the Moyer, as may be necessary.

## 15. Power and Function of the General Assembly

The Assembly shall;

1. advise the Authority on policy and strategic issues;
2. establish technical committees, as may be necessary;
3. Submit opinions on the annual performance report and other information of the Authority.

## 16. Meeting of the General Assembly

1. Regular meeting of the general assembly shall be once in a year, however; there shall be a meeting where emergency so requires;
2. There shall be quorum where more than half of the members are present;
3. Decision of the general assembly shall pass by majority vote; however, in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;
4. It may issue internal regulation of its meeting producer.

## 17. Power and Function of the Sub-City Office

1. Prepare work programme and submit to the Sub-City executive committee of food, medicine, healthcare administration and control, implement same upon approval;
2. Execute regulatory standards prepared by the Federal Government and harmonized to the existing Situation of the City;

፫.ለአንደኛ ደረጃ ሆስፒታል፣ ስፔሻል ክሊኒኮች፣ ለዲያግኖስቲክ ምርመራ ማዕከላትና ናሙና መቀበያ ፣ለመድኃኒት ቤቶች ለጥቃቅንና አነስተኛ የምግብ ማምረቻ ማዕከላትና አከፋፋዮች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

፬. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ የተዘረዘሩት ተቋማት ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች በወጣው መስፈርትና የስነ ምግባር ደንብ መሠረት መስራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፭. ለክፍለ ከተማው ተጠሪ በሆኑ ጤናና ጤና ነክ ተቋማት የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦች ፣ መድኃኒቶችና ጥሬ ዕቃዎች በአግባቡ መወገዳቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፮. በክፍለ ከተማው የሚገኙ ጤና ተቋማት የናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ የሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች እና ኘሪ ከርሰር ኬሚካሎች ለህሙማን ማዘዝን፣ ማደልን፣ አጠቃቀምን፣መመዝገብንና ሪፖርት ማድረግን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፯. በክፍለ ከተማው የጤና ነክ ተቋማት ተገቢውን የሐይጅንና የአካባቢ ጤና አገልግሎት መስፈርት ማሟላታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፰.ለህብረተሰቡ ለመጠጥ የሚቀርብ ውኃ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፱. በክፍለ ከተማው የምግብ ፣ የመድኃኒት የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ፣ የጤና ባለሙያዎች እና የጤናና የጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማትን በሚመለከት መረጃ ይይዛል ያደራጃል ለባለስልጣኑ ሪፖርት ያደርጋል፤

፲. የፅህፈት ቤቱን ሰራተኞች በከተማው የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

፲፩. የህብረተሰቡንና የግለሰብን ጤና ለመጠበቅ የድምጽ እና የአየር ብክለት ለመከላከል በፌደራል የምግብ፣ መድሀኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን በሚወጣ ደረጃ መሠረት ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣

፲፪.ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ህጋዊ ተግባሮች ያከናውናል፡፡

## ፲፰.*የክፍለ ከተማ ፅህፈት ቤት ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር*

የክፍለ ከተማው የፅህፈት ቤት ኃላፊ በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሾም ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

፩.ፅህፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል ያስተዳድራል፣

3. Issue renew, suspend and revoke certificate of competency of primary hospital, special clinics, diagnostic center and specimen collection sites, drug stores, micro and small scale enterprises food production centers and distributors;
4. Inspect and control that the health professionals working under the institution listed in sub (3) of this Article discharge their duties in accordance with the set requirements and ethical standards;
5. Follow up and control proper disposal of expired foods, medicines, and their raw materials in health and health related institution with the Sub-City;
6. Inspect and follow up distribution prescription, dispensing, use, recording and reporting of narcotic drugs psycho tropic substance and precursor chemicals, in health institutions situated in the Sub-City;
7. Follow up and control the fulfillment of necessary hygienic requirements in the health related institutions with in the sub-city;
8. Inspect and follow up that the quality of water supply for the public is up to the standard;
9. Keep and organize data as regards food, medicine, environmental health care, health professionals, health and health related institutions under control within the sub city;
10. Employ, administer and dismiss employee of the office according to the civil service law;
11. Follow up and control the implementation of sound and air pollution prevention on the basis of standard set by the Federal Food, Medicine and Health Care Administratuion and Control Authority with the view to care health of the public and private individuals;
12. Perform other legal activities that enable attain its objectives.

## 18. *Power and Function of Head of the Sub-City Office*

The head of sub city office being appointed by chief executive of the respective sub city shall have the following power and duties to;

1. direct and administer the office

፪. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፅህፈት ቤቱ ኃላፊ፡-

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፯ የተመለከቱትን የፅህፈት ቤቱን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፤

ለ. የፅህፈት ቤቱ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ. የፅህፈት ቤቱን የስራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለክፍለ ከተማው የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፤

መ. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ፅህፈት ቤቱን ይወክላል፤

ሠ. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ይሳተፋል፤

ረ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ ያረፈበትን የስራ ኘሮግራም በጀትና የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈፃሚና ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ያቀርባል፤

፫. ለፅህፈት ቤቱ የስራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከስልጣኑና ተግባሩ በሙሉ ወይም በከፊል ለፅህፈት ቤቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፉ ይችላል፡፡ ሆኖም እርሱ በማይኖርበት ጊዜ የሚወከለው ሰው ከ፴ ቀናት በላይ የሚሰራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቀርቦ መፈቀድ አለበት፡፡

## ፲፱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

ኮሚቴው፣

፩. ፅህፈት ቤቱ የሚቆጣጠራቸው ተቋማት ደረጃቸውን ጠብቀውና በተቀናጀ መልክ መስራታቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል፤

፪. ለዋና ስራ አስፈፃሚው የሚቀርበውን የፅህፈት ቤቱን የስራ ኘሮግራምና በጀት ሪፖርት ያፀድቃል፤

፫. በፅህፈት ቤት ኃላፊ በሚቀርቡለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ይወስናል፡፡



2. Without prejudice to the generality of sub article (1) of this Article, head of the Sub-City office shall;

   a. Implement power and function of the office specified under Article 17 of this proclamation;

   b. Prepare and submit annual and budget plan of the office to the executive committee; implement same up on approval;

   c. Prepare and submit annual performance and financial report of the office to the executive committee and the Director General of the Authority;

   d. Represent the office in its relation with third parties;

   e. Attend in the meeting of the executive committee;

   f. Submit financial and performance report of the office approval by the executive committee to the chief executive of the respective sub city and Director General of the Authority;

3. Delegate his powers and functions to the employees of the office partially or fully to the extent that it is necessary to facilitate works of the office, however, where the agent may work for more than 30 days, the agency shall be priory approved by chief executive of the respective sub city.

## *19. Power and Function of the Executive Committee*

The committee shall;

1. Supervise that institutions oversighted by the office are working keeping the standard and in coordinated manner;
2. Approve the work program and budget report to be submitted to the chief executive;
3. Discuss and decide on maters provided by the head of the office.

## ፳. ስለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት

፩.የኮሚቴው አባላት ፣ አግባብነት ካላቸው አካላት የተውጣጡ ሆኖ በክፍለከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰየሙ ይሆናል፤

፪.የኮሚቴው ቁጥር ፭ ወይም ፯ ይሆናል።

## ፳፩.ስለስራ አስፈጻሚ ኮሜቴ አባላት ስብሰባ

ኮሚቴው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፫ በተመለከቱት የስራ አመራር ቦርድ የስብሰባ ስነ ስርዓቶች ይመራል።

## ፳፪.የወረዳ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

፩. የወረዳ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር የሥራ ፕሮግራም በማዘጋጀት ለወረዳ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፣ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪. በፌደራል መንግስት ደረጃ ተዘጋጅተው በከተማው ነባራዊ ሁኔታ ተጣጥመው የቀረቡትን የቁጥጥር ደረጃዎች ያስፈጽማል፤

፫. በወረዳው ለሚገኙ የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ክሊኒኮች፣ የጤና ጣቢያዎች፣ የመድኃኒት መደብሮች፣ የምግብ ማዘጋጃ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተዘረዘሩት ተቋማት ላይ የሚሰሩ ባሙያዎች በወጣው መሥፈርቶችና የሥነ ምግባር ደንብ መሠረት መሥራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፭. ለወረዳው ተጠሪ በሆኑ ጤናና ጤናነክ ተቋማት የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦች፣ መድኃኒቶችና ጥሬ እቃዎች በአግባቡ መወገዳቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፮. ህገወጥ ምግብ፣መድኃኒትና የጤና አገልግሎት ይከላከላል፣ ይቆጣጠራ፣ አስፈላጊ እርምጃም ይወስዳል፤

፯. ለወረዳው ተጠሪ የሆኑ የጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት ተገቢውን የኃይጅንና የአካባቢ ጤና አገልግሎት መሥፈርት ማሟላታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል

፰. በወረዳው የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣የጤና ባለሙያዎች የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት በሚመለከት መረጃ ይይዛል፣ ያደራጃል ለክፍለ ከተማ ሪፖርት ያደርጋል፤

## 20. Executive Committee Member

1. Member of the committee shall be composed of persons extracted from relevant organization and shall be appointed by the chief executive;
2. Number of members of the committee shall be 5 or 7.

## 21. Meeting of the Executive Committee

Meeting of the committee shall be held in accordance with the procedures stated under Article 13 of this proclamation.

## 22. Power and Function of Woreda Office

1. Prepare work program of food, medicine and health care administration and control of the resection Wereda and submit to the chief executive of Wereda; implement same upon approval;
2. Execute regulatory standards prepared by the Federal Government and harmonized with the existing situation of the City;
3. Issue ,renew, suspend and revoke competency certificate of primary and medium clinics, drug stores, food processing institutions within the respective Wereda;
4. Inspect and control that the health professionals working under the institutions listed in sub Article (3) of this article discharge their duties in accordance with the set reguirements and ethics standards;
5. Follow up and control proper disposal of expired medicine, foods and their raw materials in health and health related institution accountable to the Wereda;
6. Prevent and Control illegal food, medicine and health service and take appropriate measure;
7. Follow up and control the fulfillment of necessary hygienic and environmental health service requirements in controllable health related institutions under the wereda;
8. Keep and organize data regarding food, medicine, environmental health care, health professionals and health and health related institutions in the wereda;

፱. በፌደራል የምግብና መድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ የድምጽና የአየር ብክለት ለመከላከል የሚወጣ ደረጃ በወረዳው ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፲. የወረዳውን ጽህፈት ቤት ሰራተኛ በከተማው የመንግስት አስተዳደር ህግ መሰረት ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፤

፲፩. ለሚሰጠው አገልግሎት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ክፍያ ይሰበስባል፤

፲፪.ዓላማውን ለማስፈጽም የሚረዱ ሌሎች ህጋዊ ተግባሮች ያከናውናል፤

## ፳፫.የወረዳው ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

የወረዳው የጽህፈት ቤት ኃላፊ በወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሾም ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

፩. የወረዳውን ጽህፈት ቤት በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አጠቃይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳው የጽህፈት ቤት ኃለፊ

ሀ.በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ የተመለከቱትን የጽህፈት ቤቱን ስልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል

ለ. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፣ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ.የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚና ለክፍለ ከተማው የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ጽህፈት ቤት ያቀርባል፤

መ.ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፡፡

## ፳፬.ስለ ተቆጣጣሪዎች

ባለሥልጣኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በምግብ፣ በመድሃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ላይ የሚወጡ ሌሎች ደንቦችና መመሪያዎችን ለማስፈፀም ተቆጣጣሪዎችን ይመድባል፡፡ ዝርዝር ተግባራቸውን በተመለከተ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡



9. Follow up and control the implementation of standards set by the federal food, medicine and health care administration and control Authority to prevent sound and air pollution for the protection of the public;
10. administer and control employee of the office according to the civil service law of the city;
11. Collect fee for the service it delivers in accordance with appropriate law;
12. Perform other legal activities that enable achieve its objectives.

## 23. Power and Functions of Head of Wereda Office

The head of woreda office being appointed by chief executive of the respective wereda, shall have the following power and function to;

1. Direct and administer the Wereda office
2. Without prejudice to the generality of sub article (1) of this Article the Head of the Wereda office shall;
   a. implement the powers and functions of the wereda office stated under Article 22 of this proclamation;
   b. prepare and submit annual activity and budget plan of the office and submit to the wereda chief executive; implement same up on approval;
   c. Submit annual financial and performance report to the woreda chief executive and subcity food, medicine and health care administration and control office;
   d. Represent the office in its relation with third parties;

## 24. Inspectors

The Authority or office shall assign inspectors to implement the provisions of this proclamation and other regulation and directives related with food, medicine and health care administration and control; the particular functions shall be determined by regulation issued to implement this proclamation.

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፭.የበጀት ምንጭ**

የባለሥልጣኑ ወይም የጽህፈት ቤቱ በጀት ምንጭ በከተማው አስተዳደር የሚመደብ በጀት ይሆናል።

**፳፮.የሂሳብ መዛግብት**

፩. ባለስልጣኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ህጐት መሠረት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት መያዝ አለበት፣

፪. የባለስልጣኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው ዋና ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተር በሚሰየመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**፳፯. መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ፲፭/፪ሺ፩ አንቀጽ ፳፱(፮) (፯).(፰). (፲፪).(፲፫).(፲፬) እና

፪. የጤና ቢሮ ሥልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፩ አንቀጽ ፳፱ ንዑስ አንቀጽ (፱) የጤና አገልግሎት ኘሮግራሞችን ከሚያካሄዱ መንግሥታዊ ያልሆኑ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ጋር ስምምነቶችንና ውሎችን መፈፀምንና አፈፃፀማቸውን መከታተል በሚል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ለሚያቋቁማቸው ክሊኒኮች የሙያ ፈቃድ መስጠት፣ማደስና መቆጣጠር ለባለሥልጣኑ ተላልፏል፣

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሥር ከተገለጹ ሥልጣንና ተግባራት ጋር የተያያዙ መብቶችና ግዴታዎች ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል።

**፳፰. ደንብ የማውጣት ስልጣን**

ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

**፳፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

*አዳስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም*

*ኩማ ደመቅሳ*

*የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ*

## Part Three

## Miscellaneous Provisions

***25. Budget***

The budget of the Authority or Office shall be allocated by the City Government.

***26. Books of Account***

1. The Authority or office shall keep complete and accurate books of accounts in accordance with the finance laws of the city Government;
2. The books of accounts and other financial documents of the Authority or the office shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

***27. Transfer of Rights and Obligations***

1. The right and obligation assigned to Health Bureau per Article 29/(6) (7) (8) (12) (13) (14) and.
2. Not withstanding the provision of Article 29 Sub Article 9 of proclamation No 15/2001 as regards the conclusion contracts and signing with Non Governmental charity organization that conduct programs of medical service and follow up the implementation of same issue; The renewal and inspection of professional license of clinics established by charity organization shall be transferred to the Authority;
3. Rights and obligations of the Bureau in relation to the powers and functions stated under the provisions of sub-article 1 and 2 of this Article shall be transferred to the Authority.

***28. Power to Issue Regulation***

The City Government Cabinet may issue regulation for implementation of this proclamation;

***29. Effective Date***

This proclamation shall enter into force as of its publication on the Addis Negari Gazzette.

***Done at Addis Ababa this 18th day of February, 2012***

***Kuma Demeksa***

***Mayor of Addis Ababa City***

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፭.የበጀት ምንጭ**

የባለሥልጣኑ ወይም የጽህፈት ቤቱ በጀት ምንጭ በከተማው አስተዳደር የሚመደብ በጀት ይሆናል።

**፳፮.የሂሳብ መዛግብት**

፩. ባለስልጣኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ህጐች መሠረት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት መያዝ አለበት፤

፪. የባለስልጣኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው ዋና ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተር በሚሰየመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**፳፯. መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ፲፭/፪ሺ.፩ አንቀጽ ፳፱(፮) (፯).(፰). (፲፪).(፲፫).(፲፬) እና

፪. የጤና ቢሮ ሥልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺ.፩ አንቀጽ ፳፱ ንዑስ አንቀጽ (፱) የጤና አገልግሎት ኘሮግራሞችን ከሚያካሄዱ መንግሥታዊ ያልሆኑ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ጋር ስምምነቶችንና ውሎችን መፈፀምንና አፈፃፀማቸውን መከታተል በሚል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ለሚያቋቁማቸው ክሊኒኮች የሙያ ፈቃድ መስጠት፣ማደስና መቆጣጠር ለባለሥልጣኑ ተላልፏል፣

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ሥር ከተገለጹ ሥልጣንና ተግባራት ጋር የተያያዙ መብቶችና ግዴታዎች ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል።

**፳፰. ደንብ የማውጣት ስልጣን**

ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

**፳፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

*አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም*

*ኩማ ደመቅሳ*

*የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ*



## Part Three

## Miscellaneous Provisions

**25. Budget**

The budget of the Authority or Office shall be allocated by the City Government.

**26. Books of Account**

1. The Authority or office shall keep complete and accurate books of accounts in accordance with the finance laws of the city Government;
2. The books of accounts and other financial documents of the Authority or the office shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

**27. Transfer of Rights and Obligations**

1. The right and obligation assigned to Health Bureau per Article 29/(6) (7) (8) (12) (13) (14) and.
2. Not withstanding the provision of Article 29 Sub Article 9 of proclamation No 15/2001 as regards the conclusion contracts and signing with Non Governmental charity organization that conduct programs of medical service and follow up the implementation of same issue; The renewal and inspection of professional license of clinics established by charity organization shall be transferred to the Authority;
3. Rights and obligations of the Bureau in relation to the powers and functions stated under the provisions of sub-article 1 and 2 of this Article shall be transferred to the Authority.

**28. Power to Issue Regulation**

The City Government Cabinet may issue regulation for implementation of this proclamation;

**29. Effective Date**

This proclamation shall enter into force as of its publication on the Addis Negari Gazzette.

*Done at Addis Ababa this 18th day of February, 2012*

*Kuma Demeksa*

*Mayor of Addis Ababa City*